| Process<br>Stakeholders Analysis | Expected out put<br>The planner identifies Participants in the platform; identify the need, problem and capacities of each group |
|---|---|
| Problem and potential analysis | Problems are analysed through different platforms and presented to a multi-disciplinary, multi-stakeholders conference. The platform will discuss the problems and constraints of the planning region.<br><br>Participants will identify natural, human, financial, institutional and material potentials of the spatial framework in order to put them into use for problem solving |
| Objective analysis | Participants set the objective of the program with detailed monitoring indicators. Here principles, international commitments, human rights determinations (ex. every person shall eat) will help to determine the level of indicators. At this level, usually the politicians set internationally accepted pro-poor objectives. |
| Alternative analysis | This is a critical stage, which is usually overlooked almost all the time. The planning team or any interested stakeholder should present alternative action paths to achieve commonly-stated objectives. Here is also where the major differences in approach could be observed. Mostly governments provide one option to citizens. That option is their option. Participation requires the options of various stakeholders need to be discussed, debated and consensus be established. The best way to get out from this process is to establish primarily alternative selection criteria. Goal-oriented alternative analysis approach is recommended to easily establish consensus. The platform will discuss the various recommendations and resource use plans to select few options. |
| Program formulation | Based on selected strategy and development path, a detailed description of major programmes, investment profiles and long-term implementation modalities need to be worked. While programs may be perfect in content and design, by whom and how they are implemented determines their impact on poverty. Hence negotiation of roles among stakeholders should be emphasised. |
| Monitoring strategy | Stakeholders will share responsibility to answer the questions such as who shall perform the task, for whom shall it report and etc. This part is usually forgotten. Consequently, transparency and accountability are usually lacking.<br>In a centralised system with lack of adequate monitoring and evaluation strategy involving Macro, Meso and Local interest groups, funds could easily be appropriated with false reports. |

Source: Constructed by the author.

Table 2. Instruments of Participation

| Instrument | Advantages | Disadvantages |
|---|---|---|
| Information Dissemination | Widespread information if carefully designed, different types of media to reach specific group of population. | One-way communication, not understandable by everybody if not adapted to the particular group, low capacity for feedback. |
| Public Exhibitions | Presentation of overview of specific planning proposals, alternatives, procedures prior to decision-taking; two-way communication possible. | Medium capacity for feedback, not understandable by everybody. |
| Specific diagnostic workshops | The problems and constraints of specific sectors or interest groups can easily be diagnosed and most precise problem and potential analysis can be possible through participation | Problems are narrowly defined and in a complex environment. |
| Public conference and debates | This type of conferences and debates could help to achieve a broader consensus about development issues. This could be very useful if it is handled with skilled facilitators and is organised after specific workshops. | Facilitation and consensus building requires longer period of time. |
| Community Meetings | Gathers large portions of local population, direct dialogue between planner and community, discussion of interests, problem needs. | May be dominated by local elite's, groups without lobby have no access, not guaranteed that people's opinion not taken into account. |
| Village workshop | Focus on particular location, address specific group of population, allow for interactions among villagers. | Huge resource required to cover all villagers within a rural district, result difficult to co-ordinate. |
| Public hearings | Receiving opinions, comments and proposals from the public, opinions documented as a matter of public record. | Little impact on planning if scheduled to late in the process, often only one way collection of information without interactions. |
| | | |

Source: Constructed based on the works of Poppe, 1993.

## THE ROLE OF THE CIVIL SOCIETY

The civil society should actively participate in the process. The civil society should clearly know that the government is responsible for the process and should respect their right. They should understand the rule of participation–consensus building–and hence should not say 'take as guaranteed'–that all of their views is right.

They have to work to deepen understanding of poverty, presenting alternative policy ideas, indicating participatory monitoring frameworks and negotiating roles with the government. After the approval of the strategy, civil societies should advocate for a greater debt relief measures than the measures taken by lenders and facilitate early approval by the boards of the IMF and World Bank.

## RECOMMENDATIONS

PRSP is a long-term issue. The people have all the rights in the process. The way the strategy is designed determines the content and subsequent outcomes. Better participation of different interest groups from the beginning will ensure a solid framework to design objective (based on reality, major problems of the country and inclusive) strategy. Because of this the government should redefine its role in terms of participatory principles:

- Should proactively seek stakeholders (civil societies) participation starting from the initial phases of the preparation,
- Design a participatory and bottom procedures that will allow the strategy to include problems of specific nature and group,
- Inform lower level governments, civil societies about the PRSP and proactively seek their participation,
- Institutionalise the participatory forum,
- Disseminate information to civil societies and decentralise government organs to effectively implement the PRSP process,
- Ease the legal requirement and support the mushrooming of civil societies, and finally
- Capacity-building for decentralised government structures should be emphasised.

## NOTES

1 This part was summarized ( unless mentioned) from Steifel &Wolfe,1994, PP 23 - 31

2 Please for detailed account of the definitions and applications of participation look (Matthias Stefel and Marshall Wolf, 1994.

3 Paternalistic and technocratic approaches aims to provide access to resources and institutions while withholding control.

4 When participation is viewed in terms of organized groups the implicit assumption is that these groups have defined goals and strategies to achieve their goal. The planner should work to build consensus among organized groups who may have opposite interest.

5 This could happen also in developed countries. It is usual to get two types of women groups in the US. One of the group supports of the democrats and the other group supports the republicans. The difference is that, unlike in Ethiopia, alternative forums of association are allowed in the US. The teachers association is a good example of a civil society crisis in Ethiopia.

6 Development is a process of incorporation. Old relations of production require to be regularly developed in order to fit the growing productive forces. Hence, gradual transition of informal institutions in favour of formal relations is a requirement of development itself.

7 Some people argue that in a democratic culture where governments held power through direct democracy (election) why a representative democracy such as a plat forum. The main reason is that the government represents only the majority and minorities should have a chance. In a country where a revolutionary force is in power minorities could count more. This should not be equated with the radical proponents who consider state as a problem and pursue anarchist utopia. Healthily functioning state is probably indispensable for functioning of participatory democracy and development of free market economy.

8 Most of these states in the USA have a planning advisory or commission composed of the major political parties, different interest groups and government representatives. That can be a good model for participatory governance. Nations can only be built through this process

9 The PRSP includes more stages. The Approval, the implementation and the monitoring and evaluation stages are followed after these stages. The envisaged list here constitutes the diagnostic and programming phase.

## REFERENCES

Brinkerhof, Derric and Zamor J.C. (ed.) (1986). *Politics, Projects and People: Institutional Development in Haiti.* New York.

Berand Janssen, (1996) 'Why Village Level Planning Requires District Planning: Some Arguments', Spring News.

Berand Jenssen (1993). *Planning As A Dialogue.* Bangkok.

Cernea,M.M.(ed.) (1991). *Putting People First: Sociological Variables in Rural Development.* New York,

Debebe Habtewold (2000), Food Aid and Peasant livelihood, Addis Ababa,

David Marsden & Peter Oakly (1990) 'Evaluating Social Development Projects' *Development Guidline,* No 5, Oxfam.

Esman, Milton and Norman Uphoff (1984). *Local Organisations: Intermediaries in Rural Development.* Ithaca.

Georg E. Frerks ( 1991). *Participation In Development Activities at the Local Level: Case Study from a Sri Lankan Village.* Bargsons Lt. Pakistan.

Honadle, George and Van Sant, J. (1985). *Implementation for Sustainability: Lessons from Integrated Rural Development.* Connecticut.

IDS (2001). Policy Brief 2001. ISSN, 1360-4724, also, IDS Policy Brief, April, 2001.

Johnson, B.F. and Clark, W.C. (1982). *Redesigning Rural Development: A Strategic Perspective.* Baltimore.

Lele, Uma (1982). *The Design Of Rural Development: Lessons from Africa.* Baltimore.

Matthias Stefel and Marshall Wolfe (1994). *A voice for the Excluded, Popular Participation in Development, Utopia or Necessity?* New Jersey.

Manfered Poppe (1993). *Towards an Organisational Framework for District Development Planning and Management: Planning As A Dialogue.* Bangkok.

Muller Peter, M. Program (1995) 'Management For Regional Planning', *Spring News*, Dortmund.

Peter M. Brook, Stephen Akryd and Wolday Amha (2000), Policy and Institutional Strengthening for Improved Food Security and Poverty Reduction In Ethiopia. Paper presented to the European union, (draft, November 2000).

Powel and Terey (1995), Partners in Development Conference for South Wolo. Conference Report, Bahirdar.

Rondonelli, D.A. (1990). *Development Projects as Policy Experiments: An Approach to Development administration.* London.

Uphoff, N.T. (1986). *Local Institution Development: An Analytical Source Book With Cases.* Connecticut.

Wubalem Fekadu (1995) 'Institutional Aspects Of Participation', *Spring News*, Dortmund.

Yohannes Mekonnen ( ), Institutional Aspects Of Regional Planning, Case Study on ANRS. Paper Presented To University of Science and Technology, Kumasi, Ghana.

# ስለደመወዝ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር ለቀረበው አስተያየት የተዘጋጀ መልስ እና የግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር

ከፋሲል ጣሰው
ዋና አዲተር መ/ቤት

## 1. መግቢያ

በልሣነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ 3(5) የመንግስት ሠራተኛ ደመወዝ ገቢ ግብር ሒሣብ ስሌት አሠራር በሚል ከቀረበው የተቋውሞ አስተያየት የተወሰዱ ዋና ዋና ሐሳቦች በአጭሩ፡- የደመወዝ ገቢ ግብር ክንውን ከቅርብ አመታት ወዲህ ከእቅዱ የሚበልጥ መሆኑና ለዚህም የገቢ አስተዳደሩ ቅለት አስተዋፅዖ ማድረጉ፣ በልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ 2(1) እና 3(1) የቀረበው የገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት ያተኮረው ከሥራ በሚቀሩ ሠራተኞች ላይ በመሆኑ የሒሣቡ ልዩነት ማነስና መብዛት ቁም ነገር የሚገባ ባለመሆኑ በኢኮኖሚው ላይ ያለው ተፅዕኖ በሚል ለውይይት መቅረቡ አስገራሚ መሆኑ፣ ቀጣሪው ግብሩን ቀንሶ መክፈሉ (tax withholding) በተቃራኒው በመገንዘብ (misquote) በማድረግ ፋሲል ኋላ ቀር አሠራር ነው ብሏል መባሉ፣ ቀጣሪው ከተቀጣሪው ይበልጥ ኃላፊነት እንደሚሰማው መገንዘብ ማስፈለጉን፣ የፋሲል ስጋት በየዓመቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁት የሒሳብ ባለሙያዎች ሥራ ማጣት መሆኑ፣ በአሁን ወቅት ያለው የግብር አሰባሰብ ወጭ እጅግ አናሳ መሆኑ እንደብቃት መለኪያ ተደርጎ መቅረቡ፣ ከደመወዝ ገቢ ግብር ጋር በተያያዘ ይበልጥ አስፈላጊ የሚመስለው ፅንሰ ሀሣብ የሠራተኛን የመሥራት ፍላጎት መጫኑ (distortionary) በግብር ምጣኔ ለውጥ (discretionary change) ምክንያት መሆኑ፣ ከግብር ነፃ ገቢ ብር 120 የፋሲልን የግብር ተቀናናሽ ሂሣብ ሥሌት አዛብቷል መባሉ፣ አንዱ የግብር አስተዳደር ጥራት መለኪያ የሂሣብ ስሌቱ ግልፅና ቀላል መሆኑንና ለዚህም ሠራተኛው ከሥራ ሲቀር አማካይ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት መጠቀሙ ከትክክለኛው ልዩነት ቢኖረውም ግልፅነትን የሚጠቁም መሆኑን፣ ሁለቱ የህግ ባለሙያ አስተያየቶች አወያይ መድረክ ሊሆኑ መቻላቸውንና በእነዚህ አስተያየቶች ላይ ፀሀፊው የራሳቸውን ትንታኔ በመስጠት በመጨረሻም በአሁኑ ወቅት ይበልጥ አጋጣሚው ሰፊ የሆነው የውጭ ትምህርት ከሚከታተሉ የመንግስት ሠራተኞች ግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር ሒሳብ ስሌት አሠራር መሆኑንና የዚህም ሒሣብ ስሌት ውጤት ከፍ እና ዝቅ ሊል መቻሉን አስረድተዋል።

ስለዚህ የዚህ ፅሁፍ አላማ ከላይ የተዘረዘሩትን የተቃውሞ ሐሳቦች ቀደም ሲል በልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ 2(1) እና 3(1) የቀረቡትን የደመወዝ ገቢ ግብር ሒሳብ ስሌት አሠራር ትክክል አለመሆን የጠቆሙበት አንድም ተጨባጭና አሳማኝ ነገር አለመኖሩን በቅደም ተከተል በዝርዝር ለማቅረብ ነው።

በተጨማሪ የውጭ ትምህርት እድል አግኝተው ከሚሄዱት ሠራተኞች የግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር ሒሣብ ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል የተባለው የሒሳቡ ስሌት የግብር መሠረትን፣ የሠራተኛውን የሥራ ደረጃ የሠራተኛውን ደመወዝ (በጀት) እወጃና አጠያየቅን እገናዝቦ ካለመሠራቱ የተነሣ መሆኑን በመግለፅ የግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር ወጥ የሆነና አንድ ዓይነት መሆኑን ለማስረዳት ነው።

በመጨረሻም አንድ ሠራተኛ ሙሉ ወር ሠርቶ ግብርና ጡረታ የተከፈለበትን የተጣራ ደመወዙን ባይወስድ (ባይቀበል) የሒሳቡን አመዘጋገብ ሥራ በአሁኑ ወቅት ካለው የልምድ አሠራር ጋር በማገናዘብ ተገቢውን የመፍትሔ ሐሳብ ለማቅረብ ነው።

## 2. የበጀት እቅድና ክንውን

የደመወዝ ገቢ ግብር በቅርብ ዓመታት በየዓመቱ ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘው በላይ አፈፃፀም በማሳየት ላይ ሲገኝ... የገቢ አስተዳደሩ ቀላል መሆኑ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረጉን አቶ ፋንታሁን በለው ገልፀዋል።[1] ይሁን እንጂ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው የደመወዝ ገቢ ግብር በላይ እየተሰበሰበ መሆኑ በአሁኑ ወቅት ያለውን የደመወዝ ገቢ ግብር አስተዳደር ቀላልነትና ቀልጣፋነት ሊጠቁም አይችልም። ይህንን ሃሣብ ግልፅ ለማድረግ የበጀት አቀራረብ አፀዳደቅና አፈፃፀም ሒደትን በተመለከተ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁን እና ደንቡን መሠረት በማድረግ ቀጥሎየተመለከተውን መገንዘብ ይኖርብናል። በጀት (ገቢና ወጭ) በሚመለከታቸው የህግ አስፈፃሚ አካላት በበጀት ጥሪው መሠረት በየመ/ቤቱ በጥናት ላይ ተመስርቶ ከተዘጋጀ በኋላ ከበጀት ጠሪው አካል ጋር[2] ከፍተኛ ውይይት ተደርጎበት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ለህግ አውጪው) ቀርቦ በቂ ውይይት ተደርጎበት ይፀድቃል። በዚሁ መሠረት በጀት የህግ አስገዳጅነት ባህሪውን ያገኛል። የበጀት ዕቅድ የሚባለው ይኸው ፀድቆ በነጋሪት ጋዜጣ የሚታወጀው በጀት ነው። በጀት ከታወጀ በኋላ በቀጣይነት በትክክል በተያዘለት ፕሮግራም መሠረት መፈፀሙ (መከናወኑ) ዋነኛ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህንንም የበጀት አፈፃፀም (ክንውን) በሕግ

መንግስቱ አንቀፅ 101 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚያረጋግጠውና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሒሳብ ኦዲት ሪፖርት የሚያቀርበው የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ነው። በመሆኑም ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው የደመወዝ ገቢ ግብር አንፃር የተሰበሰበው (የተከናወነው) ከበለጠ ከየት መጣ የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። ከዚሁ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በ1970 ዓ.ም ጠቅላላ የቀጥታ ገቢ ግብር ክንውን (አፈፃፀም) ከዕቅዱ መብለጡን አስመልክቶ ዋና ኦዲተሩ ባቀረቡት የኦዲት ሪፖርት ክንውኑ መብለጡ የሚያመለክተው መጀመሪያውኑ ታቅዶ የታወጀው በጀት በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ አለመሆኑን ገልፀው ነበር። ስለዚህ በጀት ከመታወጁ በፊት በከፍተኛ ጥንቃቄ በሚገባ መጠናት አለበት።[3]

## 3. የደመወዝ ገቢ ግብር በኢኮኖሚው ላይ ያለው ወይንም የሚያስከትለው ተፅዕኖ

አቶ ፋንታሁን በልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ 2 ቁጥር 1 እና ቅፅ 3 ቁጥር 1 የቀረቡት ፅሑፎች ትክክል አይደሉም ብለው ከተነሱበት አንዱ ሃሳብ የግብር ሂሣብ ስሌቱ ያተኮረው ከስራ ገቢታ በሚቀሩ ሠራተኞች ላይ መሆኑንና ነገር ግን ይህ አጋጣሚ አነስተኛ ስለሆነ በመንግሥትም ሆነ በተቀጣሪዎቹ ገቢ ላይ የሚያስከትለው ማነስና መብዛት ቁም ነገር የሚገባ አለመሆኑንና እንደውም ጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰቶት በኢኮኖሚው ላይ ያለው ተፅዕኖ በሚል ርዕስ መቅረቡ እንዳስገረማቸው አውስተዋል።

ይሁን እንጂ ከሥራ ገበታ መቅረት አጋጣሚው አነስተኛ ነው ላሉት ጉዳይ ቀደም ባሉት ፅሁፎች ላይ ከስራ የሚቀር ተብሎ የቀረበው መሠረተ ግምት (postulate) ስለግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር ወጥ የሆነ (consistent) እና ሳይንሳዊ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ነው። በመሆኑም ሠራተኛው በተለያየ ቀን ሲቀጠር ወይም የተወሰነ ቀን ሰርቶ ሥራውን ቢለቅ የደመወዝ ገቢ ግብሩ ሒሳብ የግብር መሠረቱን፣ የገቢውን እርከንና ተጓዳኝ የሆነውን የገቢ ግብር ምጣኔ አገናዝቦ በትክክል መሥራት እንዳለበት ለማስገንዘብና ይኸው ሀሳብ (idea) እንደ ኀልዮ (theory) ሆኖ እንዲያገለግል ጭምር ነው።

አቶ ፋንታሁን ከላይ እንደተጠቀሰው ... የሚያስከትለው ማነስና መብዛት ቁም ነገር የሚገባ አይሆንም ያሉት ምን አልባት የመጠኑን (materiality concept) ያነሱ ይመስለኛል። እዚህ ላይ ምን ያህል እንደሆነ በመጠን ያልገለጹት ቢሆንም መጠኑ (materiality concept) የሕግ ወይንም የፓርላሜንት የሆኑ ጉዳዮችን ሊገልፅ አይችልም። ስለዚህ የመጠኑ መብዛት ወይም ማነስ ሳይሆን ሊተኮርበት የሚገባው የግብር ህጉና የፋይናንስ አስተዳደሩ አዋጅ በሚገባ መተግበራቸውንና እንዲሁም በጀት በአዋጅ የሚወጣ እና በውስጡ የህግ አስገዳጅነት ባህርይ መያዙን ነው።

ያ ሁን እንጂ አቶ ፋንታሁን የሂሣብ አሠራር ችግር መኖሩን እምነው ነገር ግን አጋጣሚው አነስተኛ ነው ላሉት ያቀረቡት የመፍትሄ ሃሣብ የለም። በመሆኑም ችግሩን ዝም እንበለው (እንተወው) ያሉት ይመስላል። በሽታ በተገኘበት ወቅት ወዲያውኑ ካላከምነው ወደማይድን ደረጃ አይደርስም ወይ? ትንሽ ነው ያሉት አጋጣሚ አያድግም (አይሰፋም)? ቢያንስ ቢያንስ ችግሩ ሲያጋጥም የሂሳቡ ምዝገባ ሥራ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት መስተካከል እንደሚገባው መጠቆም ይገባዎት ነበር።

በተጨማሪ መንግሥት በኢኮኖሚ ፖሊሲው ዓላማ አድርጎ ከሚያነሳቸው ጉዳዮች የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት፣ ሥራ አጥነትን መቀነስ እና ዋጋ ማረጋጋት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነኝህን ዓላማዎች መንግሥት እውነት የሚያደርግበት (የሚያሳካበት) ዋና ዋና መሳሪያዎቹ (policy instruments) ደግሞ ግብር (taxation) እና ወጭ (expenditure) ናቸው። እነኝህ የፖሊሲ መሳሪያዎች በወረቀት ላይ በመለወጣቸውና በመታወጃቸው ብቻ ሳይሆን የተጠቀሱትን ዓላማዎች የሚያሳኩት በሚገባ በሥራ ላይ እንዲውሉ (implement) ሲደረጉ ነው። በመሆኑም የደመወዝ ገቢ ግብር ከቀጥታ ገቢ ግብር አንዱ ሲሆን የዚህ ግብር ሂሣብ አሠራር ትክክለኛ መሆን በኢኮኖሚው ገቢ ላይ አወንታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረውና ይኸው ግብር (tax) የኢኮኖሚው "አውራ" መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 4. የሠራተኛ ቅጥርና ግብር አከፋፈል

### 4.1. የመንግስት ሠራተኛ ቅጥር እና ግብሩን ከምንጩ ማስቀረት (withholding tax)

"አቶ ፋሲል የደመወዝ ገቢ ግብር በቀጣሪው መሰብሰብ ኋላ ቀር አሰራር መሆኑን ጠቅሰዋል" በማለት አቶ ፋንታሁን በለው በልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ 3 ቁጥር 5 ያቀረቡት የተቃውሞ አስተያየት ስህተት ነው። ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ በተጠቀሱት መፅሔቶች (ልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ 2 ቁጥር 1 እና ቅፅ 3 ቁጥር 1) የቀረቡትን ፅሑፎች በሚገባ አንብበው ካለመረዳት የተነሣ በተቃራኒው ተገንዝበው ('misquote') በማድርጋቸውና በሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ሠራተኛ ቀጣሪን ትርጉም (concept) ካለማጤን የተነሣ ይመስለኛል።

ስለዚህ ከዚህ በፊት የታክስ ፖሊሲ (የገቢ ግብር ታሪፎችን፣ እርከኖችና የግብር መሠረትን) መለወጥንና የአፈፃፀም ችግሮችን መሠረት አድርጎ የተፃፉትን ፅሑፎች በድጋሚ በሚገባ ማጤን ይኖርብናል።

በሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ሠራተኛ አቀጣጠርና ቀጣሪው ማን እንደሆነ ለመረዳት በማዕከልና የክልል አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፵፩/፲፱፹፰ ማጤን ይኖርብናል። በዚሁ አዋጅ የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን የመንግሥት ሠራተኞች አቀጣጠር ... በመንግሥት ሠራተኞች ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት እንዲፈፀም የሚያደርግና የሚቆጣጠር መሆኑ ተገልጿል። በመሆኑም የመንግሥት የባለበጀት መ/ቤቶች ኮሚሽኑ በመንግሥት በሚያስወጣቸው መመሪያዎችና ደንቦች

መሠረት ለስራ የሚፈለጉትን ባለሙያ በመገናኛ ብዙሀን ማስታወቂያ እያወጡ እያንዳንዳቸው ሲቀጥሩና ሲዋዋሉ ይስተዋላል። እዚህ ላይ የመንግሥት ሠራተኛ ቀጣሪ የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች መሆናቸውን ያስገነዝበናል። በመሆኑም እነኝሁ የተለያዩ መ/ቤቶች የሠራተኞቻቸውን ደመወዝ ገቢ ግብር ቀንሰው ለአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በቀጥታ ሲከፍሉ ነው ግብርን ከምንጩ ማስቀረት (withholding tax) በሚገባ ተከናወነ ልንል የምንችለው። ስለዚህ የገንዘብ ሚኒስቴር የራሱ ሠራተኞች ቀጣሪ ብቻ ሆኖ ሳለ እንደ አጠቃላይ የመንግስት ሠራተኛ ቀጣሪ አድርጎ መገንዘቡ ተገቢ አይደለም። ይሁን እንጂ ገንዘብ ሚኒስቴር የሌሎች የባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኛ ቀጣሪ ሳይሆን የደመወዝ ገቢ ግብርና የጡረታ መዋጮን እየቀነሰ የተጣራ ክፍያ ብቻ በመላክ እየተገበረ ያለው አሠራር ቀጥተኛ ያልሆነ ግብሩን ከምንጩ ማስቀረት አሠራር (indirect withholding tax) ሊባል ይችል ይሆናል።[4]

ይህም በመሆኑ ሠራተኛው ከሥራ በሚቀርበት ወቅት፣ የተወሰነ ቀን ሠርቶ ሥራውን በሚለቅበት ወቅት ወይም አዲስ ሠራተኛ በተለያዩ ቀናት በሚቀጠርበት ጊዜ እልፎ እልፎ ለደመወዝ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር ስህተት ምንጭ (መነሻ) ሊሆን ችሏል።[5]

### 4.2. ቀጣሪው መ/ቤት የሠራተኛውን ገቢ ግብር ቀንሶ በማስቀረት ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን የሚከፈልበት ምክንያት

ቀጣሪው የሠራተኛውን የደመወዝ ገቢ ግብር ቀንሶ እንዲከፍል የሚደረገው ለግብር አስተዳደር ቀላልነትና ሥራ እንዳይበደል ሲባል ነው። ምክንያቱም እንበል አንድ መሥሪያ ቤት ወደ 500 የሚደርሱ ሠራተኞች ቢኖሩትና የሚፈለግባቸውን የደመወዝ ገቢ ግብር እያንዳንዳቸው (በነፍስ ወከፍ) ለአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በየወሩ እንዲከፍሉ ቢደረግ ብዙ ጊዜ ሊወስድ፣ ብዛት ያለው የገቢ ደረሰኝ ሲያስቆርጥ ወዘተ የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩ እና ለሥራ ቅልጥፍና ስለማይረዳ ነው።[6] ይሁን እንጂ አቶ ፋንታሁን በለው "...ታክስ የመክፈል (የመሰብሰብ) ኃላፊነት ገቢውን ከሚያገኘው (ከደመወዝተኛው) ይልቅ ደመወዙን በሚከፍለው (ቀጣሪው) ላይ እንዲሆን መደረጉ የታክስ አሰባሰቡን ይበልጥ ኃላፊነት ሊሰማው በሚችል አካል ላይ መጣሉን መገንዘብ ያስፈልጋል" በማለት ገልፀዋል። ይኸ ግብርን የመክፈል (የመሰብሰብ) ኃላፊነት ከግብር ከፋዩ (ሠራተኛው) ይልቅ ቀጣሪው የበለጠ ኃላፊነት ስለሚሰማው ነው የሚለው ሀሣብ የመላውን ሠራተኛ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ስሜት (civic duty) የናቀ ግምታዊ አባባል ይመስላል። ይህ ከሆነ ከሌሎች ቀጥታ ገቢ ከሚያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰበሰበው የቀጥታ ገቢ ግብር እንደ እርሻ ገቢ ግብር (agricultural income tax) የንግድ ትርፍ ግብር (business profit tax) ወዘተ እንዴት ሊሰበሰብ ቻለ?

አቶ ፋንታሁን በለው ከሠራተኛው ይልቅ ቀጣሪው የበለጠ ግብር የመክፈል (የመሰብሰብ) ኃላፊነት እንደሚሰማው ከገለጹ በኋላ በሌላ በኩል ደግሞ "ይኸውም ህጉ ግዴታውን የጣለው ገቢውን ከሚያገኘው አካል ላይ በመሆኑ ተፈፃሚነቱን የጎላ ያደርገዋል" ብለዋል። ይህ ሐሳብ ገቢውን የሚያገኘው (ሠራተኛው) ቀጥታ ግብሩን መክፈል አለበት የሚል እንድምታ አለው። ይህ ደግሞ ይብሱኑ ግብሩን ቀጣሪው መ/ቤት ቀንሶ ይክፈል ከሚለው ሀሣብ ጋር ይጋጫል።

## 5. ግብር ለመሰብሰብ የሚወጣው ወጭና የሥራ ዕድል ፈጠራ

### 5.1. ግብር ለመሰብሰብ የሚወጣው ወጪ ምን ያህል መሆን አለበት?

"ከሁሉም በላይ ለገቢ አሰባሰቡ መንግሥት የሚያወጣው ወጭ እጅግ አናሳ እንዲሆን ረድቷል። በዚህ ረገድ የፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከ1986-1992 በጀት ዓመት በየዓመቱ በአማካይ የሰበሰበውን ብር 195 ሚሊዮን የሥራ ግብር ውሳኔ (እቅድ) ያከናወነው ብዛታቸው ከ6 በማይበልጡ ሠራተኞች መሆኑን መገንዘብ እንደሚቻል " አቶ ፋንታሁን የገለጹ ቢሆንም የፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ግን በ1992 ዓ.ም. "የመንግሥት ግብር አሰባሰብና ችግሮቹ" በሚል ርዕስ ያቀረበው የጥናት ፅሑፍ ላይ የግብር አሰባሰብ ወጭ (cost of collection) በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ3% - 5% ቢሆንም የባለስልጣኑ ዓመታዊ የወጭ በጀት ከሚሰበሰበው ግብር ጋር ሲነፃፀር በአማካይ 0.21% መሆኑን ነው። የባለሥልጣኑ ጥናት በመቀጠል ይህም የሚጠቁመው መንግሥት 100 ብር ለመሰብሰብ የሚመድበው የወጭ በጀት በአማካይ 0.21 (ሃያ አንድ ሳንቲም) አካባቢ እንደሆነ አውስቷል። በተጨማሪም ተቀባይነት ካለው አነስተኛ የግብር አሰባሰብ ወጭ ብር 3 (ሶስት ብር) ጋር እንኳን ሲነፃፀር የኢትዮጵያ ሃያ አንድ ሳንቲም ግድም መሆኑ የሚያመለክተው የውጤታማነትና የብቃት ምልክትን ሳይሆን በተቃራኒው ለሥራው ተገቢና አስፈላጊ የሆነ በቂ የሠው ኃይል፣ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ እንዳልተመደበና እንዲሁም ሁነኛ የሆነ የግብር አሰራር ዘዴ ያለመዘርጋቱን አብራርቷል። ከዚህም በላይ የባለሥልጣኑ ጥናት ኢኮኖሚው ሊያመነጭ የሚችለው የግብር መጠን እንዳልተሰበሰበ ይገልፃል። በመሆኑም መንግሥት ለሚሰበስበው ገቢ የሚያወጣው ወጭ እጅግ አናሳ መሆኑ መሰብሰብ ከሚገባው ገቢ (potential revenue) በታች መሰብሰቡን ከመጠቆም በስተቀር የሠራተኛ ገቢ ግብር አስተዳደር ግልፅነትና ቀልጣፋነት ሊጠቁም እንደማይችል መገንዘብ ይኖርብናል። ስለዚህ የፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ባቀረበው የጥናት ፅሑፍ መሠረት በጀቱን በማስተካከል በሰው ኃይል፣ በንብረት (material) እና በሁነኛ የግብር አሰባሰብ ዘዴ በማሟላት ማጠናከርና ማስፋፋት ይኖርብናል።

### 5.2. የሥራ ዕድል ፈጠራ (Employment Creation)

የፋሲል ስጋት በሐገራችን ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች በየዓመቱ የሚመረቁት የሒሣብ ባለሙያዎች ሥራ ማጣት ነው በማለት አቶ ፋንታሁን አውስተዋል። ይሁን እንጂ በቅይጥ ክመና (mixed economy) ሥርዓት ለሚተዳደር አገር በአሁኑ ወቅት ውድድሩ ዓለም አቀፋዊ ይዘት አለው። በመሆኑም የሠለጠነው የሠው ኃይል በዚህ ውድድር ሣቢያ ወደ ውጭ ድርጅትና ወደ ግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የመንግሥትን መ/ቤት እየለቀቀ ሲሔድ ይታያል። የዚህ ዋነኛ ምክንያት የመንግሥት ገቢ በጣም አነስተኛና ውስን በመሆኑ ለሠራተኛው ጉልበት (ሙያ) የገበያውን ዋጋ ባለመክፈሉ ይመስለኛል። በዚህ የተነሣ የመንግሥት ተቋሞች (public sectors) ተፈላጊውን ምርትና አገልግሎት በተቀላጠፈና ጥራት ባለው በበቂ ሁኔታ ለሚመለከተው ሁሉ ሊያቀርቡ (ሊሰጡ) አይችሉም። ስለዚህ ይህንን ችግር ለመግታት፣ በየጊዜው ከየትምህርት ተቋማቱ (ከዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ፣ ከኢንስቲትዩት ወዘተ) የሚመረቁትን ባለሙያዎች የሥራ ዕድል ለማስፋፋትና እንደውም ከተቻለ የሠለጠኑ ባለሙያዎችን መልሶ ለመቅጠር እና የተሻለ ለመክፈል መጀመሪያ የመንግሥትን ገቢ ማሳደግ አለብን። ይህንን ሃሣብ ደግሞ ተግባራዊ ለማድረግ በቅድሚያ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣንን በሚገባ ማጠናከርና ማስፋፋት ይኖርብናል። በመቀጠልም ሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶች መጠናከራቸውና መስፋፋታቸው አይቀርም (የግድ ነው)። የመንግሥት መ/ቤቶች የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠታቸው ደግሞ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በተጓዳኝ እንዲሁ ቀልጣፋ እንዲሆንና እንዲስፋፋ ይረዳል።[7] ስለዚህ የሥራ ዕድል ፈጠራው ለአንድ የትምህርት ሙያ ብቻ አለመሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

## 6. የግብር ምጣኔ ለውጥ፣ ከግብር ነፃ ገቢ፣ አማካይና ታዳጊ ገቢ ግብር

### 6.1. የግብር ምጣኔ ለውጥ (Discretionary Change)

የግብር ምጣኔ በሕግ ከወጣ በኋላ ቀልጣፋ በሆነ የግብር አስተዳደር ተግባራዊ እንዲሆን ይጠበቃል። ለአፈፃፀም እንዲቀል በሕጉ ከተመለከቱት የግብር ምጣኔዎች (statutary tax rates) የገቢ ግብር ማስከፈያ ፎርሙላ (tax formula) ይሠራል።[8] የገቢ ግብር ማስከፈያ ምጣኔ በሥራ ላይ እያለ በጊዜ ሒደት ኢኮኖሚው ለውጥ ሲያመጣ የሚሠበሰበው የገቢ ግብር አብሮ ሲለወጥ (built-in-flexibility) ይችላል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በአንዳንድ ሁኔታዎች ለምሳሌ በዋጋ አለመረጋጋት በሥራ አጥነት መጨመር ወይንም በግል ክፍለ ኢኮኖሚው መስፋፋት ወይም ማነስ ወዘተ በተከሠቱ ወይም በሚከሰቱ የለውጦች አስገዳጅነት መሠረት መንግሥት ለውጦቹን ለማስተካከል ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የበጀት ፖሊሲ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል። ይህም የበጀት ፖሊሲ ለወጥ የገቢ፣ ወይም የወጭ ወይም የሁለቱም ለውጥ ነው አስተዳደራዊ ለውጥን (discretionary change) የሚባለው። የግብር ምጣኔ አስተዳደራዊ ለውጥ በተመለከተ ሁለት የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉ። አንዱ አስተሳሰብ ኢኮኖሚው እያደገ በሄደ ወቅት የሚሰበሰበውም ግብር እያደገ ከሄደ የግብር ምጣኔዎች ለውጥ ማድረግ የግብር ከፋዩን ባህሪ ሊያስለውጥ ስለሚችል አያስፈልግም የሚል ሲሆን የሁለተኛው አስተሣሰብ ግን የግብር ምጣኔ ለውጥ (discretionary change) ምንም አያጣላም (አያስፈራም) መንግሥት ለግለሰቦች ግለሰቦች ለመንግሥት ተሳስበው እስከሠሩ ድረስ በግብር ከፋይ ላይ የሚፈጥረው የተለየ ባህሪይ አይኖርም የሚል ነው። ምንም እንኳን የግብር ምጣኔ ለውጦችን አስመልክቶ ሁለት የተራራቁ አስተሳሰቦች ቢኖሩም የበጀት ፖሊሲን በተመለከተ ሁለተኛው አስተሳሰብ በአብዛኛው እንደሚወሰድ ይወሳል። ምክንያቱም መንግሥት መጀመሪያውኑ የግብር ምጣኔዎች (tax rates) ለውጥ የሚያደርገው በኢኮኖሚው ለውጥ የተነሳ በመሆኑና ለውጦቹንም ለማስተካከል ሲሆን በዚሁ መሠረት ማንኛውም አስተዋይ የሆነ ህጋዊ ሰው ሁሉ መንግሥት በሚያወጣቸው ሕጎች መሠረት ስለሚሠራ በመሆኑ ነው ይላሉ።

ይሁን እንጂ አቶ ፋንታሁን በእርግጥ ማንኛውም ታክስ (ግብር) ይብዛም ይነስም ውሳኔ የማዛባት ባሀርይ እንዳለውና ...የማንኛውም የገቢ ግብር ዋና ዓላማ የመንግስትን ወጭ ለመሸፈን የሚያስችል ገቢ ማመንጨት መሆኑን ገልፀዋል። በዚሁ መሠረት እንበል በአሁኑ ወቅት ያለው የደመወዝ ገቢ ግብር ምጣኔ የመሥራት ፍላጎትን በመጠኑ ተጭኗል ስለዚህ በተወሰነ መጠን የላይኛዎቹ የግብር ምጣኔዎች ዝቅ ቢደረጉ ሠራተኛውን ብዙ እንዲሠራ ይገፋፋል ብዙ ከሠራ ብዙ ገቢ ያገኛል ብዙ ገቢ ካገኘ ደግሞ ጠቀም ያለ ግብር ሊከፍል ይችላል። በመሆኑም የመንግስት ገቢ በተሻለ ሁኔታ ያድጋል። እዚህ ላይ የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ሳይጠናከርና ሳይስፋፋ የታሰበው የገቢ ግብር እንዴት በቀላሉ ሊሰበሰብ ይችላል የሚለው ነው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ።[9,10]

### 6.2. ከግብር ነፃ ገቢ (Exemption)

አቶ ፋንታሁን በለው የፋሲልን የተቀናሽ ግብር ሒሳብ ስሌትን ያዛባው ከማንኛውም ግለሰብ ገቢ ላይ ተቀናሽ የሚሆነው ብር 120 ደመወዝ ነው ብለዋል።

ከግብር ነፃ የሆነው ገቢ ብር 120 የተቀናሽ ግብር ሒሳብ ስሌት ውጤትን ያላዛባ መሆኑን ከማየታችን በፊት ከግብር ነፃ ገቢ (exemption) የሚለውን ፅንሰ ሃሣብ ለመዳሰስ እንሞክር። በእርግጥ ማንኛውም ግብር ከፋይ ግለሰብ ግብር የሚከፍለው እንደገቢው መጠን ነው። ይሁን እንጂ ለመሠረታዊ ኑሮው ማሟያ አስፈላጊ የሆነውን ገቢ ያህል ከግብር ነፃ ቢሆን እንደሚመረጥ (The income necessities of life ought to be exempted) ይወሳል። ከግብር ነፃ መሆን ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ ለግብር ፍትሀዊነት ብቻ (a matter of equity) ሳይሆን ለግብር አስተዳደር አመችነት ጭምር (a matter of administration expediency) ሲባል መሆኑ ይታወቃል። ምክንያቱም

አነስተኛ ገቢ ያገኘ ግለሰብ በተቻለ መጠን ያገኘውን ገቢ የመሠረታዊ ኑሮውን ወጭ የሚሸፍንበት በመሆኑና ለግብር የሚከፍለው ገንዘብ ስለማይኖረው ነው በእርሱ መከፈል የነበረበትን ግብር ሌሎች የተሻለ ገቢ ያገኙ ግለሰቦች እንዲከፍሉ የሚደረገው። በዚህ አስተሳሰብ ነው አነስተኛ ገቢ ያለው ግለሰብ ግብር እንዲከፍል የማይጠየቀው። መንግሥት ግለሰቦችን አነስተኛ ገቢ ያላቸውንም ሆነ ሀብታሞችን በአንድ ዓይን የሚያይ በመሆኑ የሚያወጣቸው ህጎች ለማንኛውም ዜጋ እኩል ተፈፃሚ ናቸው። በዚሁ መሠረት ብር 120 ከማንኛውም ደመወዝተኛ ከወር ገቢው ከግብር ነፃ ይሆናል። ስለዚህ የግብር መሠረቱ ብር 980 የሆነ የወር ደመወዝተኛ ብር 120 የያዘው የገቢ እርከን ከግብር ነፃ መሆኑ፣ ከብር 121 እስከ ብር 600 ላለው የገቢ እርከን በ10% የግብር ምጣኔ ብር 48 እና ከብር 601-980 ላለው የገቢ እርከን በ15% የግብር ምጣኔ ብር 57 በድምሩ ብር 105 ግብር መክፈሉ እኔ ያቀረብኩትን የገቢ ግብር ሒሳብ ስሌት ያዛባበት ምንም ዓይነት ሁኔታ የለም። ይህንን ሀሣብ ግልፅ ለማድርግ የሚከተለውን ግለሰቡ በወር ውስጥ የሚከፍለውን ግብር የቀናት ገቢው ጥገኛ መሆኑን የሚያሳየውን ምስል (ሀ) እንመልከት።[11] የወሩ ቀናት በቅደም ተከተል በውስጠ አዋቂ (implicitly) በገቢው (ደመወዙ) አቅጣጫ በምስሉ ላይ መኖሩን እንርሳ።

$$\text{ግብር} = (Y_h - 0)0\% + (Y_i - 120)10\% + (Y_j - 600)15\%$$

$$0 < Y_h \leq 120 ፣ 120 < Y_i \leq 600 ፣ 600 < Y_j \leq 980$$




ምስል (ሀ) የወሩ ገቢ ግብር የየቀኑ የደመወዝ ገቢ መጠን ውጤት መሆኑን የሚገልፅ ሥዕል[12] ግብር ከላይ ወደ ታች ያለውን አቅጣጫ የሚያሳይ ሲሆን ደመወዝ ከግራ ወደ ቀኝ ያለውን አቅጣጫ ያሳያል። ምንጭ ልሳን ኢኮኖሚ ቅፅ 3(1) ገፅ 39.

## 6.3. የአማካይ ገቢ ግብር (Proportional Income Tax) እና የታዳጊ ገቢ ግብር (Progressive Income Tax)

...የአንድ ታክስ አስተዳደር ጥራት ከሚለካባቸው መስፈርቶች መካከል ስሌቱ ቀላልና ግልፅ መሆኑ ነው። በዚህ ረገድ ከሥራ ገበታቸው የተለዩ ሠራተኞች ላልሰሩበት ቀናት የሚደረገው የገቢ ስሌት አማካይ ግብርን በመውሰድ ስለሆነ ግልፅ ያደርገዋል በማለት አቶ ፋንታሁን አስረድተዋል።

አማካይ ገቢ ግብር የሚባለው አንድ ሰው (ግለሰብ) በየትኛውም ገቢው ላይ በመቶኛ የሚከፍለው የገቢ ግብር እኩል መሆኑን ሲሆን ነገር ግን የታዳጊ ገቢ ግብር የሚባለው አንድ ሰው ገቢው ባደገ ቁጥር በመቶኛ የሚከፍለው የገቢ ግብር ማደጉን ነው። በመሆኑም የብር 980 የወር ደመወዝተኛ በየወሩ የደመወዝ ገቢ ግብር ብር 105 ይከፍላል። ይህም የደመወዝ ገቢ ግብር በአማካይ ገቢ ግብር ምጣኔ (proportional tax rate) 10.7% ወይም በታዳጊ ገቢ ግብር ምጣኔዎች (marginal tax rates) ለምሣሌ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ባለው የወር ገቢ ግብር ህግ መሠረት እስከ ብር 120 ድረስ ያለው ገቢ ከግብር ነፃ፣ ከብር 121 እስከ ብር 600 ድረስ ያለው የገቢ እርከን በ10% ግብር ምጣኔ ብር 48 እና ከብር 601 እስከ ብር 980 ድረስ ላለው የገቢ እርከን በ15% የግብር ምጣኔ ብር 57 በመጠቀም ሊሰራ ይችላል። ስለዚህ የታዳጊ ገቢ ግብር ሒሳብ አሠራር ጊዜ ይወስዳል፣ ይከብዳል፣ ወዘተ በመሆኑም የአማካይ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት ይቀላል ለማለት ከፈለጉ በእርግጥ ሊቀል ይችል ይሆናል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ቀጥታ ገቢ ግብር ሕግ ታዳጊ ነው እኮ! አማካይ የገቢ ግብር ሒሣብ ስሌት አሠራር የመጠቀም ሥልጣን የለንም።[13] በመሆኑም በገቢ ግብር ሕጉ ያልተቀመጠውን አሠራር ሠርተን ለገቢ ግብር አስተዳደር ቀላልነትና ግልፅነት በሚል ከግብር ሕግ እና ከፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ውጭ ልንሆን አንችልም። በእርግጥ በታዳጊ ገቢ ግብር የተሠራውን የገቢ ግብር ሒሳብ አቶ ፋንታሁን እንዳሉት ከሥራ ገበታቸው የተለዩ ሠራተኞች ላልሠሩበት ቀናት የሚደረገው የግብር ስሌት አማካይ ግብሩን በመውሰድ ስለሆነ ቀላልና ግልፅ መሆኑንና ውጤቱም ከትክክለኛው ሒሳብ ስሌት ልዩነቱ መጠነኛነቱን የገለጹበት ሃሳብና ይኸው አሠራር ትክክል መሆኑን የፋሲል ሒሳብ አሠራር ያመለክታል ብለው በሌላ በኩል ደግሞ የፋሲልን የገቢ ግብር ሒሳብ ስሌት "ያዛባው" ብለው ካሉት ሃሣብ ጋር እርስ በእርሱ ይጋጫል። ስለዚህ በግብር ሕጉ መሠረት የደመወዝ ገቢ ግብርን ሒሣብ ስናሠላ መጠቀም ያለብን የታዳጊ

ገቢ ግብር ታሪፎችን (marginal tax rates) ብቻ መሆን አለበት።

## 7. የሕግ አማካሪዎች አስተያየት

አቶ ፋንታሁን በለው የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የሕግ አማካሪዎች የሠጡትን አስተያየት እዚህ ላይ ማንሳቱ የተለየ የውይይት መድርክ ሊፈጥር እንደሚችል ገልፀው አስተያየቱን ለማብራራት ሞክረዋል። ይሁን እንጂ የሕግ አስተያየቱ እርሳቸው በተነተኑት መልኩ ሳይሆን የሚተረጎመው ከዚህ እንደሚከተለው ነው። በሕግ አስተያየቱ መሠረት አንድ ሰው ግብር ሊከፍል የሚገባው ባገኘው ገቢ ላይ ብቻ መሆኑን በመግለፅ፤

7(1). "ሠራተኛው ወሩን በሙሉ መሥራት ሲገባው አሞኛል ብሎ ካለሀኪም ፈቃድ፤ በስንፍና ወይም በሌላ ሥራ ምክንያት የተወሰኑ ቀኖችን ባይሠራ ግብሩ ሠራተኛው በሥራ በቆየባቸው ቀናት ላይ ይታሰብ" የሚለው ትክክለኛና ሊረጋገጥ የሚችል ሐሳብ (proposition) ነው። በየትኛው ቀናት ነው ሠራተኛው ያልሰራው ብለን እንድንጠይቅና እንድናውቅ ያደርገናል። በመሆኑም የሠነፈባቸው (ከሥራ የቀረባቸው) ቀናት እንበል ወር በገባ በመጀመሪያው፤ በመካከለኛው ወይም በመጨረሻው ወይም ደግሞ በተለያዩ ቀናት ተጓዳኝ የሆኑትን (የተያያዙትን) የገቢ ግብር እርከን(ዎች) እና የግብር ምጣኔ(ዎች) በማስተዋል በልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ (2) ቁጥር (1) እና ቅፅ (3) ቁጥር (1) በተተነተነው መሠረት ሒሣቡን ማስላት ይኖርብናል።

ነገር ግን አቶ ፋንታሁን ቀናት የሚለውን ለቀን ቁጥር ብዛት ብቻ በመውሰድ የሠሩት ሒሣብ ትክክል አይደለም። የብር 980 የወር ደመወዝተኛ ግለሰብ 10 ቀን ባይሠራ ከ20 ቀን ገቢው ብር 653.33 ላይ "0.15-42"[14] የሚለውን የግብር ማስከፈያ ፎርሙላ ተጠቅመው [(0.15 (653.33)-42)] ብር 56 ግብር መክፈል እንደሚገባው ገልፀዋል። በዚሁ ሂሳብ አሠራር መሠረት የ10 ቀን ገቢው ብር 326.67 ግብር የማይከፈልበት በመሆኑ "0.10Y-12" የሚለውን የግብር ማስከፈያ ፎርሙላ በመጠቀም ብር 20.67 ከግብር ተመላሽ ይሆናል ማለት ነው። የተከፈለውን ብር 56 እና ተመላሽ የሚሆነውን ብር 20.67 ስንደምረው የሚሠጠን ሒሳብ ብር 76.67 ሲሆን ነገር ግን በገቢ ግብር ሕጉ መሠረት የወር ደመወዝተኛው ከብር 980 ገቢው የሚከፍለው ግብር ብር 105 ነው ልዩነት ብር 28.33 ያሳያል[15] ።

7.2. በሁለተኛ ደረጃ "ሠራተኛው በጥፋት የተወሰኑ ቀኖች ደመወዝ ባይከፈለው ግብሩ በወሩ ጠቅላላ ገቢ ላይ ተሠልቶ ከሚደርሰው ሒሳብ ላይ ተቀናሽ ይደረግ" የሚለው የሕግ አስተያየት ግልፅ ነው። አንድ ሠራተኛ 30 ቀን ሠርቶ ነገር ግን ባጠፋው ጥፋት መሰረት የዲሲፒሊን ቅጣት እንበል አስተዳደሩ (management) የ10 ቀን ደመወዝ ቢቀጣው ሒሳቡ እንዴት ሊሠላ ይችላል?

በመጀመሪያ ደረጃ ሠራተኛው የ30 ቀን ገቢውን ያሀል የሠራ በመሆኑ የደመወዝ ገቢ ግብሩና የጡረታ መዋጮ የሙሉ ወር ደመወዙ ድርሻ ይከፈላል። ስለዚህ የቅጣት ሂሣብ ከዚህ በኋላ የሚመጣና ከሠራተኛው የተጣራ ገቢ ድርሻ ላይ የሚቀነስ ነው። ለምሳሌ የብር 980 የወር ደመወዝተኛ የ10 ቀን ደመወዙ ብር 326.67 ቢቀጣ ለእርሱ ይደርስ ከነበረው የተጣራ ተከፋይ ብር 835.80 ላይ በመቀነስ ግብር ነክ ባልሆኑ ገቢዎች ማለትም በልዩ ልዩ ገቢ ሥር የመንግሥት ሠራተኞች መቀጫ በሚል በገቢ ይመዘገባል።[16] በመሆኑም አቶ ፋንታሁን ቅጣቱን ከግብር ጋር ቀላቅለው ሒሳቡን በማስላት አሠራሩ ምን ያሀል በመ/ቤቶች የተለመደ ለመሆኑ ጥናት ይጠይቃል ያሉት በፍጹም ትክክል ያልሆነ አስተያየት ነው።

## 8. የውጭ ሀገር ትምህርት ወይም ከአንድ ወር በላይ ሥልጠና አግኝተው ለሚሔዱ የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ገቢ ግብር ሒሳብ አሠራር

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 107/1987 መሠረት የደመወዝ ገቢ ግብር ማስከፈያ ሠንጠረዥ (schedule) ገቢው ባደገ መጠን የሚከፈለው የገቢ ግብር ማደጉን ያመለክታል። ሠንጠረዡ ከተለያዩ የገቢ እርከኖች (income brackets) ጋር ተጓዳኝ የሆኑትን ታዳጊ የግብር ምጣኔዎች (marginal tax rates) ይዟል። በዚሁ የገቢ ግብር ሕግ መሠረት የብር 980 ወር ደመወዝተኛ ግብር አከፋፈል በሠንጠረዥ (1) በልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ (2) ቁጥር (1) ተገልጿል። በዚሁ ሠንጠረዥ (1) መሠረት ደመወዝተኛው ወር ለሠራበት ለሥራ ገቢ ግብር ብር 105 [(600 - 120) 10% + (380) 15% ]፡ ለጡረታ ብር 39.20 (4% 980) በድምሩ ብር 144.20 ተቀንሶ የተጣራው ብር 835.80 ለእርሱ ይከፈለዋል።

ቀደም ሲል የመንግሥት ሠራተኞች የውጭ ሀገር ትምህርት ዕድል አግኝተው ሲሄዱ ለመጀመሪያው 6 ወር ሙሉ ደመወዝ፤ ለቀጣዩ 6 ወር ግማሽ ደመወዝ ተከፍሎ ሲያበቃ ክፍያው ይቆም ነበር። የደመወዝ ክፍያው በሚቋረጥበት ወቅት የትምህርቱን እድል ያገኙት ግለሰቦች ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ ከሆነ በትምህርት ሒደቱ ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ እና እንዲሁም በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚፈጥረውን የኑሮ ጫና በመገንዘብ መንግሥት ከግንቦት 1, 1990 ዓ.ም. ጀምሮ የውጭ ሀገር ትምህርት አግኝተው ለሚሔዱ የመንግሥት ሠራተኞች እስኪመለሱ ድረስ የግማሽ ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው አድርጓል።

በመሆኑም እንበል የብር 980 የወር ደመወዝተኛ ግለሰብ የውጭ ሀገር ትምህርት እድል ቢሰጠው የግማሽ ወር ተከፋይ ደመወዙ (የጥቅሉ፣ የግብሩ፣ የጡረታውና የተጣራው) ሒሳብ ስሌት ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ (9)[17] መሠረት መሠራት አለበት።[18]

| ተከፋይ ግማሽ ደመወዝ በጥቅል | ግማሽ ግብር ተከፋይ | ግማሽ የጡረታ ተከፋይ[19] | ግማሽ የተቀናናች ድምር | ግማሽ የተጣራ ተከፍያ |
|---|---|---|---|---|
| 980÷2 = 490 | 105÷2= 52.50 | 39.20÷2 = 19.10 | 144.20÷2 = 72.10 | 835.80÷2 = 417.90 |

[9]

የማይከፈለው የግማሽ ደመወዙ (ጥቅል፣ ግብር፣ ጡረታና የተጣራው) ሒሣብ ስሌት በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ (10) ማስቀመጥ ይቻላል።

| የማይከፈል ግማሽ ጥቅል | የማይከፈል ግማሽ ግብር | የማይከፈል ግማሽ ጡረታ | የማይቀናነስ ግማሽ ድምር | ግማሽ የተጣራ |
|---|---|---|---|---|
| 980÷2 = 490 | 105÷2 = 52.50 | 39.20÷2 = 19.10 | 144.20÷2 = 72.10 | 835.80÷2 = |

(10)

| ግማሽ ደመወዝ በጥቅል | የግብር ምጣኔ | ግብር ተከፋይ | ጡረታ ተከፋይ (4%) | ተቀናናሽ ድምር | የተጣራ ግማሽ ደመወዝ ተከፋይ |
|---|---|---|---|---|---|
| 0-120ግብር የማይከፈለው | 0 | - | 4.80 | 4.80 | 115.20 |
| 121-490 370 | 10% | 37 | 14.80 | 51.80 | 318.20 |
| ድምር 490[20] | | 37.00 | 19.60 | 56.60 | 433.40 |

[11]

የሒሣቡን ሥሌት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ግማሽ ተከፋይ ሠንጠረዥ (9) ሲደመር የማይከፈል ሠንጠረዥ (10) እኩል ይሆናል ስልጠና ባይሔድ የሚከፈለውን የሙሉ ወር ደመወዝ ሠንጠረዥ (1) በየዓይነቱ [(ልሳነ ኢኮኖሚክስ ቅፅ (2) ቁጥር (1)]

ነገር ግን አቶ ፋንታሁን እንዳሉት በአሁኑ ወቅት የዚህ ዓይነቱ የትምህርት ዕድል ለሠራተኞቻቸው በሚደርሣቸው ወቅት መ/ቤቶች በአማራጭ የግማሽ ደመወዙን ሂሣብ እንዴት እንደሚያሰሉት ቀጥሎ ከተመለከተው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል።

በዚህ ሂሣብ ስሌት መሠረት የግማሽ ደመወዙ ግብር ብር 37.00፣ የጡረታ ብር 19.60 እና የተጣራ ተከፋይ ብር 433.40 ነው። ይህንን የግማሽ ደመወዝ ሒሳብ ሥሌት ውጤት እጥፍ ብናደርገው ግብር ብር 74.00 ጡረታው ብር 39.20 (ትክክል ነው) እና የተጣራው ተከፋይ ብር 866.80 ይሆናል።[21] ነገር ግን የብር 980 የወር ደመወዝተኛ በገቢ ግብር ህጉ መሠረት በሠንጠረዥ (1) እንደተገለፀው የገቢ ግብሩ ብር 105፣ ጡረታው ብር 39.20 እና የተጣራው ተከፋይ ብር 835.80 ነው። ወይንም በየወሩ ከግማሽ ደመወዙ የተጣራ ብር 417.90 መከፈል ሲገባው በሥህተት ብር 433.80 የሚከፈል በመሆኑ ልዩነት ብር 15.80 እላፊ ይከፈለዋል። እንዲሁ የግማሽ ወር ደመወዙ ገቢ ግብር በህጉ መሠረት ብር 52.50 መሆን ሲገባው ብር 37 ብቻ በመታሰቡ በየወሩ ብር 15.50 ለመንግስት መከፈል የሚገባው ግብር ሳይከፈል ይቀራል።[22] ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰውን የገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር ስህተት ለመግታትና አቶ ፋንታሁን በገለጹት መሠረት የዚህ ዓይነቱ ሂሣብ በዛ ያለ እንደመሆኑ መጠን በአገር አቀፍ ደረጃ ይኸው የሂሣብ አሠራር በማይተገበርበት አካባቢ በሠርኩላር መልክ ቢበተን የተሻለ ይመስለኛል። በተጨማሪ ወደፊት ግብሩን የሠራተኛው ቀጣሪ መ/ቤት በቀጥታ ለአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የሚከፈልበት ሁኔታ ቢመቻች የዚህ አይነቱ የገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር ስህተት እንዳይከሰት ያስችላል። ምክንያቱም ግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ከግብር አስገቢው መ/ቤት ጋር በሚገባና በቀጥታ ሂሳቡን ስለሚተሳሰብ ነው። በመሆኑም የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣንን በሚገባ ማሻሻል፣ ማጠናከርና፣ማስፋፋት ይኖርብናል።

## 9. የደመወዝ ገቢ ግብርና የጡረታ መዋጮ የተከፈለበትን የተጣራ ደመወዝ ሠራተኛው ባይቀበል ሂሣቡ እንዴት ሊስተናገድ ይግባዋል?

በአሁኑ ወቅት ገንዘብ ሚኒስቴር የሚሠራበት የሒሳብ አያያዝ ሥርዕት የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ሥርዕት (cash basis) መሆኑ ይታወቃል። ከዚህም የምንረዳው ማንኛውም ገቢና ወጭ (receipts & payments) የሚመዘገበው ገቢው ሲሰበሰብና ወጭው ሲከፈል ነው። በመሆኑም ለመንግሥት ሠራተኛ የሚከፈለው ደመወዝ ከገንዘብ ሚኒስቴር በበጀት ተጠይቆ ሲመጣ መ/ቤቱ የደመወዝ ገቢ ግብሩን፣ ጡረታውንና የተጣራ ተከፋዩ በየሒሣብ አርዕስቱ ተደልድሎ ሲያበቃ በገቢ ይመዘገባል። በመቀጠልም የሠራተኛው ጥቅል ደመወዝ የወጭ ሒሳብ አርዕስት ተሰጥቶት እንዲሁ በወጭ ይመዘገባል። ሠራተኛው ደመወዙን ከወሰደ ሒሣቡ

በዚሁ ምዝገባ መሠረት ሪፖርት ይደረጋል።

ነገር ግን አንድ ሠራተኛ እንበል የብር 980 የወር ደመወዝተኛ የሥራ ግብርና ጡረታ (ብር 144.20) የተከፈለበትን የተጣራ ደመወዙን (ብር 835.80) ሳይቀበል ቢቀር ሒሣቡ እንዴት ሊስተናገድ ይገባዋል? ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት በአሁኑ ወቅት ያለው አሠራር ምን እንደሚመስል በአጭሩ እንቃኝ። ሠራተኛው የተጣራ ደመወዙን (ብር 835.80) ካልወሰደ በልምድ የምዝገባውን አንዱን ክፍል ብቻ የወጭውን በመንካት ማለትም የወጭ ተመላሽ (ገቢ) በማድረግ ይህንኑ ገንዘብ ከመደበኛው ሒሣብ ጋር በመቀላቀል ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ ይደረጋል። ሠራተኛው (ወኪሉ) በመጣ ወቅት በመሥሪያ ቤቱ በኩል በድጋሚ ከገንዘብ ሚኒስትር በደብዳቤ የተጣራውን ተከፋይ ይጠየቅና ሲከፈለው በወጭ ይመዘገባል።

ይሁን እንጂ አንድ ሠራተኛ ግብርና ጡረታ የተከፈለበትን የተጣራ ደመወዙን ሳይቀበል ቢቀር የሒሳቡን አንድ ክፍል ብቻ በመንካት የወጭ ተመላሽ (ገቢ) ብሎ መዝግቦ ገንዘቡን ፈሰስ ማድረግ አግባብነት የለውም። ምክንያቱም ገንዘቡ የመንግሥት ገቢ ሳይሆን የግለሰቡ በመሆኑና ሠራተኛው (ወኪሉ) መጥቶ ደመወዙን መውሰዱ አይቀርምና ነው። በመሆኑም የደሞዝ ወጪን በተመለከተ ሠራተኛው ሙሉ ወር መሥራቱ ከተረጋገጠ የሒሣብ ምዝገባ መስተካከል መኖር የለበትም። ስለዚህ የሠራተኛው የተጣራ ደመወዝ ድርሻ (ገንዘቡ) ብቻ በአደራ ሂሣብ መልክ በሞ/85 መስተናገድ ይኖርበታል።[23] ስለዚህ የመንግሥት ያልሆነን ገንዘብ (ገቢ) ከመደበኛ ሂሣብ ጋር በመቀላቀል ለጊዜውም ቢሆን የግለሰቡ (የሠራተኛው) ገንዘብ ፈሰስ መደረግ የለበትም። አለበለዚያ መንግሥት ለዚህ ገንዘብ ፈሰስ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ለግለሰቡ እስከሚከፈለው ድረስ ላለው ጊዜ ወለድ (interest) ማሰብ ሊኖርበት ነው።

## 10. ማጠቃለያ

የደመወዝ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት ሲሠራ በቀጥታ ገቢ ግብር ሕጉ በደሞዝ ገቢ ግብር ማስከፈያ ሠንጠረዥ (schedule) በተገለጹት የገቢ እርከኖች (income brackets) እና በተጓዳኝ ታዳጊ የግብር ምጣኔዎች (marginal tax rates) መሠረት በመጀመሪያ የሠራተኛው የሙሉ ወር ደመወዝ ገቢው ከግብር ነፃ ገቢ (exemption) ጀምሮ በየትኛው የመጨረሻ ገቢ እርከንና የግብር ምጣኔ ላይ እንደሚወድቅ አገናዝቦ የወሩን የገቢ ግብር ሂሣብ መስራት ከዚያ ሠራተኛው ከወር በታች ቢሠራ ማለትም ከሥራ ቢቀር ወይም ቢለቅ አሊያም አዲስ ቢቀጠር ወዘተ... ከሙሉ ወር ሂሣቡ ውስጥ የሠራበትን ቀናት አጢኖ የግብሩን ሂሣብ ማስላት ይገባል።

የግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራርን በተመለከተ መንግስት የውጪ ሀገር ትምህርት ዕድል አግኝተው ለሚሄዱ የመንግሥት ሠራተኞች ከሄዱበት ተልኮ እስኪመለሱ ድረስ ግማሽ ደመወዛቸው እንዲከፈል አዝዟል። ይህም ሲሆን የሠራተኛው የስራ ደረጃ (መደብ) በግማሽ ዝቅ ይበል አለማለቱ ግልፅ በመሆኑ መሥሪያ ቤቶች የሠራተኛውን ደመወዝ በበጀት የሚያሲዙት በሙሉ ወር ደመወዙ ነው። ከሙሉ ወር ደመወዙ የሚከፈለው የገቢ ግብር ደግሞ መጀመሪያውኑ በገቢ ግብር ሕጉ መሠረት የተሠራ ነው። ስለዚህ ግማሽ ደመወዝ ይከፈል ማለት የጥቅል ደመወዝ ግማሽ፣ የተጣራ ተከፋይ ደመወዝ ግማሽ፣ የደመወዝ ገቢ ግብር ግማሽ ....ወዘተ ማለት እንደሆነ ግልፅ በመሆኑ ሂሣቡን በየአይነቱ እንዳለ ለሁለት እኩሌታ በማካፈል መሠራት ይኖርበታል።

የመንግሥት ሠራተኛ ሙሉ ወር ሰርቶ ግብርና ጡረታ የተከፈለበትን ደመወዙን ካይወስድ ቢቀር የሠራተኛው የተጣራ ገቢ ድርሻ በአደራ ሂሣብ መልክ በመሥሪያ ቤቱ በኩል የሚያልቅበት ሁኔታ መፈጠር አለበት እንጂ የመንግሥት ያልሆነን ገቢ ከመንግሥት በጀት ጋር ቀላቅሎ ወደ ማዕከል ግምጃ ቤት ፈሰስ ማድረግ አግባብነት የለውም። ምክንያቱም ሠራተኛው (ወኪሉ) መጥቶ ገንዘቡን መውሰዱ አይቀርምና ነው።

በመጨረሻም አቶ ፋንታሁን በአጠቃላይ ለሠጡት አስተያየት፣ የህግ ባለሙያዎቹ የሠጡትን የሕግ አስተያየት ነጥቦችና የግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር ሂሣብ ስሌት አሠራር ሁኔታን ለውይይት በማቅረብ የበኩልዎን አስተዋፅዖ ስላደረጉ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርና በራሴ ሥም የተለመደውን ምስጋና አቀርባለሁ።

## ዋቢ ምርሎዎች (REFERENCES)

Burgess, R and Stern, N (1993) 'Taxation and Development,' *Journal of Economic literature* Vol. XXI.

Dernburg, F and Dernburg, D (1972). *Macroeconomic Analysis: An Introduction to Comparative Static and Dynamics.* USA: Addison -Wesley Publishing Company. Inc.

Fassil Tassew (2000), Performance of Direct Taxes in Ethiopia, Unpublished M.Sc. Thessis, AAU.

Herber, B.P. (1996). *Modern Public Finance.* University of Arizona: IRWIN INC.

Ministry of Finance Annual Budgetary Revenue and Expenditure Accounts, various years.

Musgrave, R.A (1959). *The Theory of Public Finance.* New york: McGraw-Hill.

Shrivastava, O.S. (1996). *Economics of Growth Development and Planning.*

Tekle Tadesse and Djene Aredo (1994) 'Glossory of Economic Terms,' *Ethiopian Journal of Economics* 3(2).

ፋሲል ጣሰው (1999) 'የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ ገቢ ግብር ሒሣብ ሥሌት አሠራር በኢኮኖሚው ላይ ያለው ተፅዕኖ'፣ ልሳን ኢኮኖሚክስ 2(1).

ፋሲል ጣሰው (2000) 'የመንግሥት ሠራተኛ

ደመወዝ ገቢ ግብር ሒሣብ ሥሌት አሠራር ማብራሪያና ታሪካዊ ሂደት በኢትዮጵያ፣ ልሳን ኢኮኖሚክስ 3(1).

ተሻሽሎ የቀረበ የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን (1987 ዓ.ም.)

ኤፍሬም የማነብርሀን (1973) ስለሕግ መግቢያ ሕግ ፋኩልቲ

የመንግሥት ግብር አሰባሰብና ችግሮቹ በዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል የተዘጋጀ ፓናል (ፕሮሲዲንግስ) አ.አ. 1992 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በመንግሥት ወደ ውጭ ሀገር ለትምህርት ወይም ስልጠና ተልከው ትምህርታቸውን ስለሚከታተሉ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ አከፋፈል ቁጥር ጠ 80 - አጠ 52/01/09 ሚያዚያ 20, 1990 ዓ.ም.

የገንዘብ ሚኒስቴር የወሩ መደበኛ ገቢ እና ወጭ ሒሣብ ማጠቃለያ ቅፅ ገ/ሂ/29/1-2

የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የሒሣብ ኦዲት መመሪያ 1977 ዓ.ም አ.አ

የዋናው ኦዲተር የመንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ በጀት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት 1978 ዓ.ም አ.አ

ነጋሪት ጋዜጣ 20ኛ ዓመት ቁጥር 13, 1953 ዓ.ም.

ለጋሪት ጋዜጣ 22ኛ ዓመት ቁጥር 15, 1955 ዓ.ም.

ነጋሪት ጋዜጣ 1ኛ ዓመት ቁጥር 1, 1986 ዓ.ም.

ነጋሪት ጋዜጣ 52ኛ ዓመት ቁጥር 26, 1986 ዓ.ም.

ነጋሪት ጋዜጣ 54ኛ ዓመት ቁጥር 3, 1987 ዓ.ም.

ነጋሪት ጋዜጣ 3ኛ ዓመት ቁጥር 14, 1989 ዓ.ም.

ነጋሪት ጋዜጣ 3ኛ ዓመት ቁጥር 46, 1989 ዓ.ም.

## ተቀፅላ 'ሀ'

የግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር ሂሳብ ሥሌት የየቀናት ገቢ ውጤት መሆኑን ለመገንዘብ ግብር የወር ገቢ ጥገኛ መሆኑን የሚያመለክተውን እኩልታ (equation) ለሁለት በማካፈል መሥራት ይቻላል።

$$\text{ግብር} = (Y_h - 0)0\% + (Y_i - 120)10\% + (Y_j - 600)15\% \qquad [1]$$

$$\frac{\text{ግብር}}{2} = \left[\frac{Y_h - 0}{2}\right]0\% + \left[\frac{Y_i - 120}{2}\right]10\% + \left[\frac{Y_j}{2}\right]15\% \qquad [2]$$

የብር 980 ደመወዝተኛ ሙሉ ወር ይሠራል ብለን ብንገምት

$Y_h =$ ብር 120፣ $Y_i =$ ብር 600 እና $Y_j =$ ብር 980

የሚሆኑ ሲሆን እነኝህኑ ቁጥሮች በእኩልታ (2) ውስጥ ብናሥገባቸው ከዚህ የሚከተለውን የግማሽ ደመወዝን ገቢ ግብርን ሂሳብ ውጤት እናገኛለን:-

$$\left[\frac{120-0}{2}\right]0\% + \left[\frac{600-120}{2}\right]10\% + \left[\frac{980-600}{2}\right]15\%$$

$$\text{ግማሽ ግብር} = 0 + 24 + 28.50$$

$$= 52.50$$

## ተቀፅላ 'ለ'

ከላይ በተቀፅላ 'ሀ' የተመለከተውን እኩልታ(2) ቀጥሎ በተመለከተው ምስል 'ለ' የግማሽ ደመወዝ ገቢ ግብር የየቀናት ግማሽ ደመወዝ ገቢ ውጤት መሆኑን መመልከት ይቻላል።

$$\frac{\text{ግብር}}{2}=\left[\frac{Y_h-0}{2}\right]0\%+\left[\frac{Y_i-120}{2}\right]10\%+\left[\frac{Y_j-600}{2}\right]15\%$$

$$0 \langle Y_h \le 120 \quad 120\langle Y_i \le 600 \quad 600\langle Y_j \le 980$$




ምሥል ለ፤ የወሩ ግማሽ ደመወዝ ግብር የቀናት የግማሽ ደመወዝ ገቢ መጠን ውጤት መሆኑን የሚገልፅ ምስል። ግድለቱን (slope) በምንለካበት ጊዜ በደመወዝ አቅጣጫ ያለው ገቢ በሁለት መካፈል እንዳለበት እንዘንጋ::

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ዘመኑ የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ የተስፋፋበት ወቅት በመሆኑና ኢትዮጵያም የዚሁ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆኗ በውጭ ሀገር በመንግሥት ለትምህርት ተልከው የሚሄዱትን ግለሰቦች የእለት ተእለት ሁኔታ ለማወቅና ለመከታተል ብዙ አስቸጋሪ አይሆንም በሚል ግምት ነው።

---

[1] የሠራተኛው ደመወዝ ገቢ ግብር የሚሰበሰበው (ክንውኑ) ይሰበሰባል ተብሎ ከሚታቀደው መብለጡ በቅርብ ዓመታት ብቻ የተከሰተ ሳይሆን ወትሮም የነበረው ነው። ለምሳሌ ከ1963 - 1983 በጀት ዓመት ባለው 22 ዓመታት ውስጥ ከ4 በጀት ዓመት በስተቀር የ18ቱ ክንውኑ ከዕቅዱ ይበልጣል።

[2] የመደበኛ በጀት በገንዘብ ሚኒስቴር፣ የካፒታል በጀት በኢኮኖሚና ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ይጠራል።

[3] በእርግጥ የበጀት ዕቅድ ተጠንቶ የሚቀርብበት ጊዜ 6 ወር አካባቢ ብቻ መሆኑ የበጀት እቅድና ክንውን ልዩነት እንዲኖረው አስችሎ ይሆናል። ስለዚህ ከሌሎች አገሮች ልምድ እንደምንረዳው የበጀት ጥናትና ዝግጅት ጊዜ ከ6 ወር ወደ 18 ወር ከፍ ቢደረግ የበጀት እቅድና ክንውን ልዩነት እንዳይኖር ይረዳል።

[4] በገቢ ግብር ህግ ቁጥር 173/1953 ላይ በነሐሴና በጳጉሜ ወር የሚገኘው ገቢ እንድነት ተደምሮ ሊታሰብ የሚገባው እንደ አንድ ወር ገቢ ብቻ ነው ይላል። ይህም የነሐሴ ወር ገቢ ከጳጉሜ ወር ጋር ተደምሮ የደመወዝ ገቢ ግብሩ መከፈል እንዳለበት የሚጠቁም መሆኑን ያስገነዝባል። ይሁን እንጂ በጳጉሜ ወር ሠራተኛው ደመወዝ ስለማያገኝ መንግስትም ከዚሁ ከጳጉሜት ወር የሠራተኛ ገቢ ግብር አያገኝም። ነገር ግን የሠራተኛው ደመወዝ ገቢ ግብር በቀጥታ ለአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በቀጣሪው መጸቤት በኩል የሚከፈል ቢሆን ኖሮ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ይህንኑ የጳጉሜን ወር ገቢ በነሐሴ ወር ገቢ ላይ እየደመረ ግብሩን ይጠይቅ ነበር። በዚሁ መሠረት መ/ቤቶች ለጳጉሜት ወር የደመወዝ በጀት እያሳያዙ ከነሐሴ ወር ደመወዝ ገቢ ጋር በመደመር ለመንግስት ተጨማሪ ግብር ይከፈል ነበር። ይህ እየተደረገ ቢሆን ኖሮ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በተሻለ ሁኔታ እያደገ ይሔድ እንደነበር መገመት አያዳግትም። ይህንን ሀሣብ ከኢኮኖሚክስ ቲዎሪ ስናየው እውቁ እንግሊዛዊ ኢኮኖሚስት John Keynes, አጠቃላይ ፍላጎትን ሲተነትን (aggregate demand analysis) መመገብ የገቢ ጥኛ መሆኑን [c=f(Y, MPC)] አስቀምጧል። በዚህ ቲዎሪ መሠረት የሠራተኛው ፍላጎት የየቀኑን ገቢ ያህል መመገብ ነው ብንል የጳጉሚት ወር ገቢው (Y) ዜሮ ነው። ገቢው ዜሮ ከሆነ ምግቡም ዜሮ ሆነ ማለት ነው። $C= f(Y) \Rightarrow C=f(o)=0$ ይሁን እንጂ የጳጉሜትን ወር ሠራተኛው ይመገባል። በተጨማሪ የጳጉሚት ወር በእርግዝና ወቅት እንደሚቆጠር የሀይማኖት ሊቃውንቶች ያስተምራሉ። ማስገንዘቢያ ኢትዮጵያ የራሷ ቀን አቆጣጠር ስላላት ከአውሮፓ የቀን አቆጣጠር ጋር ማነፃፀር የለብንም።

[5] መ/ቤቶች ከሚያሳውጁት የመደበኛ በጀት ውስጥ ለሰራተኛ የሚከፍሉትን የተጣራውን ደመወዝ ከገንዘብ ሚኒስቴር በየወሩ ሲለቀቅላቸው የእያንዳንዱን ሠራተኛ ሥራ ግብርና የጡረታ መዋጮ ጨምሮ በየገቢ እርዕስቱ በገቢ ይመዘግቡና ከዚያ ሠራተኛው ሙሉ ወር ሠርቶ የተጣራ ደመወዙን ሲቀበል ሂሣቡ በጥቅል በወጭ ተመዝግቦ ሪፖርት ይደረጋል። ነገር ግን ሂሣቡ በዓይነት በገቢ ከተመዘገበ በኋላ ሠራተኛው ያልሠራበት ቀናት ታስቦ የተጣራው ተከፋይ በእግካይ ከወጪ ተመላሽ ሲደረግ የሥራ ግብር እና የጡረታው ተቀናናሽ ሂሣብ በገቢ ተመላሽነት አይመዘገብም። ለዚህም የባለበጀት መ/ቤቶች በአብዛኛው የሚሠጡት ምክንያት ተቀናናሹ ሂሳብ ተቆርጦ የቀረውና

የተከፈለው በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል በመሆኑና እንርሱ ዘንድ ሒሳቡ (ገንዘቡ) ባለመምጣቱ ነው። ይሁን እንጂ የሂሳብ ምዝገባውን ማስተካከል (correcting entry) መሥራት ይኖርባቸዋል።

6 የግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን የገቢ ግብር የሚሰበሰበው መንግስት ባወጣው የመደበኛ የሥራ ሰዓት ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ እያንዳንዱ የሌላው መጰቤት ሠራተኛ በዚሁ መደበኛ የሥራ ሰዓት የመጰቤቱን ሥራ ያከናውናል። ነገር ግን የሚፈለግበትን ግብር ለመክፈል ሠራተኛው በሥራ ሠዓት በንፍስ ወከፍ ቢሔድ በየመ/ቤቱ ሥራ ሊበደል ይችላል። በመሆኑም እነዚህን ሥራ ሊበድሉ የሚችሉ ችግሮችን ለማስቀረት ሲባል ነው ቀጣሪው ግብሩን ቀንሶ እንዲከፍል የሚደረገው።

7 የመሠረተ ልማት አውታሮች (infrastuctures) ምሰሶ (መሠረት) የሆነውን የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣንን በማጠናከርና በማስፋፋት ተገቢውንና ተናፋቂውን የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እንችላለን።

8 በሥራ ላይ ካለው የደመወዝ ገቢ ግብር ሕግ ሠንጠረዥ አምስት የደመወዝ ገቢ ግብር ማስከፈያ ፎርሙላዎች ተሠርተዋል።
$0.10Y_{\gamma}-12=T_{i}$ ፡ $0.15Y_{\chi}-42=T_{i}$፣ $0.24Y_{h}-102=T_{i}$ $0.3Y_{\lambda}-302=T_{i}$ እና $0.4Y_{\mu}-602=T_{m}$ ናቸው Y የሙሉ ወር ደመወዝ ገቢ ማለት ሲሆን፣ T ግብር ነው።

9 መንግሥት ግብር ይሰበስባል (ገቢ) ከዚያ በተገቢው ሁኔታ ያወጣል (ወጭ)። ገቢ ማሰባሰብ እንደ ደም ቅዳ፣ ወጭ ደግሞ ደም መልስ እንደማለት ብንወስደው፣ የደም ቅዳና የደም መልስ ሥራዎች እንደሚታወቀው የሚከናወኑት በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች (የግራ የደም ቧንቧ ሲቀዳ የቀኛ ደም ቧንቧ ይመልሳል) ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የደም ቅዳ ሥራ (ከግለሰቦች ላይ ግብር ሲያሰባስብ) በሌላ በኩል የገንዘብ ሚኒስቴር የደም መልስ ሥራ (ወጭውን) ያከናውን እንደማለት ነው። እዚህ ላይ የአንድ ሰው የደም ዝውውር በአንድ በኩል ብቻ ባለው የሰውነት ክፍል ቢሆን ጤንነቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም። በመሆኑም የአገር ውስጥ ቀጥታ ገቢን (direct taxes) የማሳሰቡን ሥራ ለአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ሙሉ በሙሉ መሥጠት ያለብን ይመስለኛል።

10 የታክስ ፖሊሲያችን በመለወጡ እኮ ነው ይህ ክርክር የመጣው። በመሆኑም ከፖሊሲው ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ አሠራሮች የግድ ያሳፈልጋሉ። ለምሳሌ የኒቨርሲቲዎች በጣም ጉብዝ የሆነን ተማሪ ለሌክቸረርነት መርጠው ያስቀራሉ ሌሎች ተተኪ ትውልዶችን እንዲያስተምር። በተመሳሳይ ሁኔታ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ይህንን ዓይነት ዕድል ማግኘት አለበት። ጥሩ ጥሩ ጎበዝና ተቆርቋሪነት (altrustice motive) ያላቸውን ምሁሮች እየቀጠረ ሥራውን የሚያስፋፋበት ሌላው ደግሞ የመጰቤቶች ትስስር (institutional integration) ይጎለብታል። ተናቦ መስራት ይመጣል፡ እየተሻሻሉና በአዲስነት እየወጡ ያሉ ሕጎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ይጀምራል። ምሁር ሁሉ ወደ እዚህ ይሰማራል። አንድ ሰው ቡና ቤት ገብቶ የሻይ ዋጋ ተሳስቦ እንደሚከፍል ሁሉ ከመንግስት የሚፈለግብትን ግብር እንዲሁ ተሳስቦ መክፈል ይጀምራል። ለምን የግብር አስከፋዩ ባለስልጣን ልክ የግል ነጋዴው የሻዩን ሒሳብ እንዳስከፈለ ሁሉ ግብሩንም ወዲያውኑ ያስከፍላልና ነው።

11 ደመወዝ (ገቢ) (Y) መነሻና መድረሻ ለሌለው ጊዜ (time) ጥገኛ በመሆኑ በተወሰነ ጊዜም የቀጣይ ተለዋዋጭ (continuous variable) ባህሪ አለው። ስለዚህ የገቢ ግብር (income tax) የገቢ ጥገኛ በመሆኑ እንዲሁ ቀጣይ ተለዋዋጭነት ባህሪ ይኖረዋል።

12 በገቢው መጠን ልክ በወሩ ቀናት ውስጥ የሚከፈለው ግብር ይለያያል። እስከ ብር 120 ድረስ የተሰራበት ገቢው ከግብር ነፃ ሲሆን ከዚያ በየቀኑ መስራት ሲቀጥል ገቢው በየቀናቱ ከግብር ነፃ ገቢ እርከን ወደተለያዩት ሁለቱ ተከታታዮች የገቢ እርከኖችና የግብር ምጣኔዎች በማደግ በ30ኛው ቀን ገቢው ብር 980 ሲሆን ብር 105 ግብር ይከፈልበታል።

13 የታዳጊ ገብ ግብር አስፈላጊነት ለገቢ ሥርጭት ፍትሀዊነት (income redistribution) ሲባል ሲሆን የአማካይ ገቢ ግብር ተጠቀምን ማለት የገቢ ሥርጭትን ፍትሃዋነት እናሳ አደረግነው ማለት ነው።

14 Y ማለት የመቀጠሪያ (የሙሉ ወር) ደመወዝ ነው። በመሆኑም ይህ የግብር ማስከፈያ ፎርሙላ የሚያገለግለው 30 ቀን ሰርቶ ሙሉ ደመወዙን ለሚያገኝ ሠራተኛ ብቻ ሲሆን ከወር በታች ለሠራ ሠራተኛ ፎርሙላውን መጠቀም አንችልም። ምክንያቱም ፎርሙላው በገቢ ግብር ሕጉ ላይ የተሠራው በወር ደመወዝ መሠረት በመሆኑ ነው።

15 ይህ የአቶ ፋንታሁን የግብር ሂሳብ አሠራር እቶ ተገኘወርቅ ገብረ በልሳን ኢኮኖሚክስ 2(5) ካቀረቡት የደመወዝ ገቢ ግብር ሂሳብ አሠራር ተቃራኒው ገጽታ ነው።

16 የየወሩ መደበኛ ገቢ ሒሳብ መስታወቂያ በክፍል 1 (በቅፅ ገሂ/29/1) ላይ በገቢ ሒሳብ መደብ ቁጥር 1702 የመንግሥት ሠራተኞች መቀጫ በሚል ተገልጿል።

17 በልሳን ኢኮኖሚክስ ቅፅ (2) ቁጥር (1) ሠንጠረዥ (8) ላይ የሚቀጥል ነው።

18 ምክንያቱም የውጭውን ትምህርት ያገኘው ሠራተኛ የሥራ ደረጃና መደቡ ስለማይለወጥ መጰቤቱም የሠራተኛውን በጀት የሚያሲዘው በሙሉ ወር ደመወዙ በመሆኑ ነው።

19 የግለሰቡ የጡረታ ተከፋይ የሙሉ ወር ደመወዙ ብር 39.20 ቢሆን ይመረጣል። ስለዚህ ብር 19.10 ከተጣራው የሰራተኛው ማግኛ ተከፋይ ላይ በተጨማሪ ቢቀነስ (ቢቆረጥ) የተሻለ ይመስለኛል። ምክንያቱም ግለሰቡ ትምህርቱን ጨርሶ ሲመለስ ያልተከፈለውን የማግኛን ጡረታ መዋጮ ጨምሮ እንዲከፍል ሊጠየቅ ስለሚችል ነው።

20 የውጭ ሀገር ትምህርት ያገኘው ግለሰብ የወር ደመወዙ ብር 980 ሲሆን የሥራው ደረጃ አሁን ባለው በመንግሥት ሠራተኞች የሥራ መደብ መሠረት ፕሮፌሽናል ሳይንስ ደረጃ 4 (ፕሣ 4) ይባላል። ግለሰቡ ግማሽ ደመወዙ ይከፈለው ሲባል ደረጃው ዝቅ ይበል ሳይሆን በሠንጠረዥ (9) በተመለከተው መሠረት ሂሣቡ መሠራት አለበት። ነገር ግን የዚህን ግለሰብ ደመወዝ ግማሹን እንደግብር መሠረት ወስደን ለብቻው ብር 120 ቀንሰን የግብር ምጣኔውን 10% ብቻ ስናደርገው የግለሠቡን የሥራ ደረጃ ወደ መለሥተኛ ፕሮፌሽናል (መፕ) ወይንም ከብር 600 በታች ተቀጣሪ አደረግነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሊሆን አይችልም።

21 ዋናው የሒሳብ አሠራር መርህ አለማዳላት (unbiasedness) ሲሆን የገቢ ግብር ሒሣብ ሥሌት በሚሠራበት ወቅት የግብር መሠረት፣ የገቢ እርከኖችን እና የግብር ምጣኔውችን በሚገባ መሠረት አድርጎ የተሠራን ሂሣብ ውጤት ግማሹ ብቻ ይከፈል ከተባለ የግብር መሠረቱን ሳንለውጥ ሂሣቡን ማስላት ይኖርብናል (ተቀጽላ 'ሀ' እና 'ለ' ተመልከት)።

22 ግማሽ ደመወዝ እንዲከፈል ያዘዙ ደንብ ስለዝርዝር ሂሳብ አሠራር የማያብራራ ቢሆንም የሂሣቡ ስሌት ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል በማለት አቶ ፋንታሁን የሠጡት አስተያየት ትክክል አይደለም። ምክንያቱም የህግ አወጣጥ ቲዎሪ ሀጎች (ደንቦች) በሚወጡበት ወቅት በአብዛኛው ጊዜ የሚመለከቱትን ሰፊ ጉዳይ ዝርዝር በሙሉ የማይዙ ሊሆኑ መቻላቸውን ያስተምረናል። በመሆኑም ህግ ሁሉንም ነገር ይዞ እንዲወጣ መጠበቅ የለበትም። ስለዚህ የሒሳብ ባለሙያዎች (Accountants) በአካባቢያቸው ያሉትን የህግ ባለሙያዎች (ልአወያጠረስ) እና የምጣኔ ሐብት ባለሙያዎች (Economists) የሙያ ድጋፍ በመጠየቅ ሂሣቡን ሊሰሩ ይገባል (የሕግና የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ግብርን በተመለከተ እንዲሁ የሒሳብ ባለሙያዎችን እያማከሩ ሊሰሩ ይገባል)። ወደፊት ዩኒቨርሲቲዎች የግብርን (Taxation) ሁኔታ በተመለከተ የህግ ሙያ፣ የሂሣብ ሙያ እና የምጣኔ ሀብት ሙያ በአንድነት ለእያንዳንዱ ባለሙያ በሚገባ ከተግባር ጋር እያቀናጁ የሚያስተምሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል።

23 ዋ/85 (የመያዣ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ) በአብዛኛው የሚሠራበት በሆስፒታሎችና ፍርድ ቤቶች ሲሆን ደረሰኙ ያስፈለገበት ምክንያት ከተያዘው ገንዘብ የተወሰነው ላስያዘው ክፍል ወይም ግለሰብ ሊመለስ የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩ ነው። እዚህ ላይ የሠራተኛው የተጣራ ደመወዝ በሞዳ85 ይስተናገድ ስንል በአደራ ሒሳብ ተቀምጦ ሠራተኛው ሲመጣ ሙሉ በሙሉ ይከፈለው ለማለት እንጅ ገንዘቡ በመያዣነት ይጠበቃል ማለታችን አይደለም።

**THIS BULLETIN AND OTHER PUBLICATIONS OF EEA ARE SPONSORED BY FRIEDRICH EBERT STIFTUNG OF GERMANY (FES), EMBASSIES OF UK, SWEDEN, NORWAY, FINLAND AND THE AFRICAN CAPACITY BUILDING FOUNDATION (ACBF).**

# *Just pay less than 20 Birr and You will have Your 'Economic Focus' for the whole year !!*

*Make sure to look for your latest 'Economic Focus' at:*



- African Bookshop
- Book Center at AAU
- The Book World
- Ghion Hotels
- MEGA Bookshops
- Meseret Nega Stationery
- Alemu Shop (Near ECA)
- Hadia Supermarket
- Twins Supermarket
- Seyoum Shop (Near Kazanchis TOTAL)
- Hill-Belt Restaurant
- Semien Hotel
- Universal Bookshop

**PRICE BIRR 3.50**

LESAN Printing Press